# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

## ተስፋ ሰጪው በራስ የመጠገን አቅም

እንደምን ሰነበታችሁ ውድ አንባቢያን! ባለፈው ሳምንት ጽfከፋችን "የመንትዮቹ ኃይል ማመንጫዎች ውልደትና አሁናዊ ቁመና" በሚል ርዕስ ፋና ወጊ ተብለው ከሚጠቀሱ የውሃ ኃይል ማመንጫዎች መካከል ስለአዋሽ 2 እና 3 ግድቦች ከፊል ገጽታ ማስነበባችን የሚታወስ ነው:: ጣቢያዎቹ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ ሕያው ሆነው እንዲቆዩ እና ዛሬም ድረስ ሥራቸውን በአግባቡ እንዲያከናውኑ ያደረጋቸውን ምስጢርን በዛሬው ዝግጅታችን እንዲህ አቅርበንላችኋል::

ወደ ጉዳያችን ተንደርድረን ከመግባታችን በፊት ቀደም ሲል የተቋሙ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች በራስ አቅም ሥራዎችን እያከናወኑ ወጪን ለመቀነስ ወይም ገቢን ለማሳደግ የሚያደርጉትን ተስፋ ሰጪ ሥራዎች ማስነበባችንን እናስታውሳችሁ::

ተቋሙ በኃይል ማመንጫና ማከፋፈያ ጣቢያዎች እንዲሁም በከፍተኛ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮች ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን እየፈተሸ በራሱ የሰው ኃይል ምላሽ መስጠትን ዛሬ አንድ ብሎ የጀመረው ጉዳይ አይደለም:: ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተቋሙ ያሉ አቅሞችን በመለየት በእያንዳንዳቸው የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ግንባታዎችና ጥገናዎች ላይ እንዲውሉ እንደተቋም ስትራቴጂ ነድፏል:: የኃይል ማመንጫዎች ኦፐሬሽን ዘርፍ በሁሉም የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች በራስ አቅም ውጤታማ የጥገና ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል:: ተቋሙ ለጀመረው የራስ አቅም አጠቃቀም ስትራቴጂ ውጤታማነት ዕድሜ ጠገቦቹ የአዋሽ 2 እና 3 የውሃ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ማሳያዎች ናቸው::

የአዋሽ 2 እና 3 የውሃ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ተወካይ ኃላፊ እና የጥገና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ሮቤል አበበ እንደሚያስረዱት፤ ግድቦቹ ሲገነቡ በአማካይ ለ50 ዓመታት አገልግሎት ይሰጣሉ በሚል ጥናታዊ እሳቤ ነበር:: እነዚህ አንጋፋ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች በየጊዜው በሚደረግላቸው የቅድመና ድሕረ ፍተሻ ክትትል እንዲሁም የጥገና ሥራ ዛሬም ድረስ ኃይል የማመንጨት አቅማቸው ሳይደክም ለብሔራዊ የኃይል ቋት የኃይል ልግስና ሥራቸውን እየከወኑ ይገኛሉ::

ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎቹ ዕለታዊ ሥራቸው እንዳይስተጓጎል እና ደህንነታቸው ዘለቄታ እንዲኖረው ተቋሙ በሚከተለው የአሠራር ስታንዳርድ መሠረት የንብረት ቁጥጥር ዘዴ "Asset control system" ተግባራዊ ይደረጋል:: በተለይም የማመንጫ ሲስተሞች በኃይል ማመንጫ ሥራ ክፍል ዕለታዊ ክትትል የሚደረግላቸው መሆኑን የጠቆሙት ኢንጂነር ሮቤል በጥገና ክፍሉ ደግሞ ሳምንታዊ፣ ወርሐዊ፣ የሦስት ወር፣ የስድስት ወር፣ የአንድ ዓመት እና የሁለት ዓመት የፍተሻ ሥራዎች ወቅቱን ጠብቀው ይከናወናሉ:: ይህም ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት ቀድሞ ለማወቅና ድንገተኛ ችግሮች ሲከሰቱ ደግሞ አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የሚያግዝ ነው:: ጣቢያዎች እያንዳንዳቸው ከ12 እስከ 14 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም ያላቸው ሁለት ሁለት በድምሩ አራት የኃይል ማመንጫ ዩኒቶች ያሏቸው ሲሆን በየጊዜው በሚደረግላቸው የፍተሻና ጥገና ሥራ ላለፉት ስድሳ ዓመታት ኃይል የማመንጨት ተልዕኳቸውን በብቃት እየፈጸሙ ይገኛሉ::

እንደ ኢንጂነር ሮቤል ገለጻ፤ ከዋናው መሥሪያ ቤት ለጥገና ሥራው ጥቅም ላይ የሚውሉ የመለዋወጫ መሣሪያዎች ይቀርባሉ፤ አንዳንድ ጊዜ እንደሥራው ክብደት በተቋሙ ካለው ቴክኒካል ድጋፍ መምሪያ ጋር በመነጋገርና በመተባበር ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ይደረጋል:: ነገር ግን አብዛኛው ሥራ በጣቢያው ሠራተኞች



የማሽኖች ደህንነት በሙያተኞች ሲረጋገጥ

አማካኝነት ይከናወናል:: ይህም ሠራተኛው በሥልጠና እና በረጅም ጊዜ ተሞክሮው ባገኘው ዕውቀት እየታገዘ አበረታች ውጤቶች እየተመዘገቡ ስለመሆናቸው ማሳያ ናቸው ብለዋል:: በተለይም አዳዲስ ሠራተኞችን ከነባሮቹ ጋር በማጣመር ልምድ እንዲያገኙ ማድረግና ጥገናዎቹ መቼ እንደተፈጸሙ በጥገናው ምን ለውጥ እንደተገኘ የሚያስረዱ መረጃዎችን ሰንዶ በመያዝ በቀጣይ ለሚሠሩ ሥራዎች መነሻ እንዲሆን እና ለቦታው አዲስ የሆኑ አካላት በቂመረጃ እንዲያገኙ መደረጉ ለውጤታማነቱ ምክንያት መሆኑን ተናግረዋል::

ኢንጂነር ሮቤል እንደሚገልጹት በመንትዮቹ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች በተደጋጋሚ ጥገና የሚደረግላቸው ጀነሬተርን ለማቀዝቀዝ አገልግሎት የሚሰጡ ራዲያተሮች ናቸው:: ራዲያተሮች የማቀዝቀዝ ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ሁል ጊዜ ፍተሻ እና ጥገና ይደረግላቸዋል:: ይህም ጀነሬተሮቹ ኃይል የማመንጨት ሥራቸውን በአግባቡ እንዲያከናውኑ ያስችላል:: የጥገና ሥራዎቹን በራስ አቅም ማከናወን መቻሉ ከፍተኛ ወጪን ያስቀረና የጥገናው ተከታታይነት ለማሽኖቹ ሕልውና ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳደረገ ኢንጂነሩ ይገልጻሉ::

ከዚሁ ጋር በተያያዘም ለጣቢያው ጥቅም የሚውሉ ፓምፖችም በተመሳሳይ መንገድ እየተጠገኑ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል:: አዋሽ በተፈጥሮው ድፍርስ እንደመሆኑ ተርባይነሮች በአፈር እንዳይበሉና እንዳይቆሽሹ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ መሠረት እየወጡ ይጸዳሉ:: ከኃይል ማመንጫ ኦፐሬሽን ቴክኒካል ቡድን ጋር በመተባበር የጣቢያውን ደህነንት የሚያስጠብቁ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን የተናገሩት ኢንጂነር ሮቤል፤ ቀደም ሲል በክፍት ሉፕ ‹‹open loop›› ሲስተም አማካኝት ውኃው ሳይጣራ ወደ ዋሻው ይገባ የነበረውን በዝግ ሉፕ ‹‹close loop›› እያጣሩ የማስገባት ሥራ መጀመሩን ተናግረዋል::

ከተወሰኑ ዓመታት በፊት በኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች አገልግሎት የሚሰጡ ማሽኖችን በዚህ ልክ መጠገን የማይታሰብ እንደነበር የተናገሩት ኢንጂነሩ፤ አብዛኛዎቹ ሥራዎች ዓመታትን ፈጅተው የውጭ ባለሙያዎችን ይጠብቁ እንደነበር ገልጸዋል:: አሁን ግን ተቋሙ ከውጭ ባለሙያ ጥገኛነት ተላቆ በራሱ አቅም እየከወነ ይገኛል:: ይህ ተቋሙ የያዘውን አዲስ ስትራቴጂ ሠራተኛው እችላለሁ! ሥራው የእኔ ነው! የሚል በራስ የመተማመን መንፈስ እንዲላበስ አስችሎታል::

ጣቢያዎቹ ዘመን ያስቆጠሩ እንደመሆናቸው አንዳንድ ሲስተሞቻቸው ኋላ ቀሮች ናቸው:: ይህንም ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር ለማጣጣም ወደፊት የመልሶ ግንባታ ሥራዎችን በመሥራት ተርባይኖችና ማሺኖች በተሻለ አቅም እንዲሠሩ ለማድረግ ጥናት እየተደረገ መሆኑን ነግረውናል::

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል